መስከረም 23 ቀን 2004 ዓ.ም

# አዬ - ዓይጋ!

**ከ አያልነሽ**

ከሁሉ በላይ በቅድሚያ አቶ ፅጌ ሀብተማርያም ከእስር የመፈታታቸውን ዜና ስሰማ የተሠማኝ ደስታ ልክ አልነበረውም። የደስታዬ ምንጭና መነሻ ደግሞ መጀመሪያውኑ እኚህ አባት መታሠር አይገባቸውም ከሚል ፅኑና ቋሚ ከሆነው እምነቴ በመነሳት ነው። ምን ይደረግ ዛሬ፣ ዛሬ እነዚህን መሰል አዛውንቶች እንዳይታሠሩና መከራን እንዳይገፉ ለማድረግ ይቻለን የነበረው ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ለታሰሩና ለተሰወሩ ዜጎቻችን ሁሉ እኩል ሁላችንም አልቅሠን፣ ጮኸን በነበረ ዛሬ የምናየውን መከራ አንደግመውም፣አናየውም ነበር። ያ አልሆነምና አሁን ሁላችንንም አንድ በአንድ እየነካ ስሜታችንንም መጉዳቱ አልቀረም። ዛሬ የእኚህን አባት መንገላታት ስምለከት በእውነቱ የሚሰማኝ ኃዘን ቀላል አይደለም - ልብንም ያደማል። ዳሩ ግን ይሄ እንዳይሆን ማድረግ ስንችል ያልተቻለን ለምንድን ነው ...? ጥያቄው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ይመለከታልና ወደኋላ ላይ በሠፊው ለማብራራት እሞክራለሁ።

ወያኔ እንደነገረን ከሆነ ለእኚህ አባት መታሠር ምክንያት በ2008 ዓ.ም ተሞከረ በተባለ (ኩዴታ) ሰበብ መሆኑ አይዘነጋም። ይህ ራሱ ተሞከረ የተባለው "**ኩዴታ**" ያልተጨበጠ ከመሆኑም በላይ ወያኔም ግርግሩን በጣም ሊጠቀምበት ሞክሯል። ከዚህ "**ኩዴታ**" ጋር በተያያዘም እስከአሁን ድረስ ታሥረው ገና ያልተፈቱ ዜጎች እንዳሉን ይታወቃል። የበደሉ በደል ደግሞ ቆርጦ ቀጥሉ ዓይጋ ያማረበት ይመስል፣ የኚህን አባት መፈታት አስመልክቶም እንዲህ ብሎ ሊያስነብብን መብቃቱ የምፀት ምፀት ነው። እጠቅሳለሁ፡

> "አቶ ፅጌ ሀበተ ማርያም ከእሥር ሊፈቱ የቻሉት በዋናነት በሠሩት ወንጀል ተፀፅተው፣ ለይቅርታ ቦርድ አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው" ይልና ኃፍረት የለሹ ዓይጋ ከ80 ዓመት በላይ የሆኑ ሽማግሌን በማንገላታት-ግዳይ የጣለ ይመስል፣ እንዲህ እያለም ሲዘባርቅ ይታያል። "የይቅርታ ቦርዱ..." ይላል ዓይጋ፥ "የይቅርታ ቦርዱ ግለሰቡ በዕድሜ የገፉና በህመም የሚሠቃዩ በመሆናቸው፣ የበደሉትንም ህዝብ ለመካስ ቃል በመግባታቸው፣ እንዲሁም በማረሚያ ቤቱ የነበራቸውን ሥነ ምግባር በማጤንም ይቅርታ እንዲደረግላቸው ለኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት ሃሳቡን አቅርቧል"

ይላል የዓይጋ አሳፋሪ ዘገባ።

በመሠረቱ እነዓይጋ እና ለገሠ ዜናዊ ይህን ዓይነት አሳፋሪ ድርጊት እንደ ጀብዱ ቆጥረው ማቅራራታቸው፣ ሁሌም ባዶ ሠብዕናቸውን ለመደበቅ ያስችላቸው ዘንድ ነውና አያስደንቅም። "**ዘባራቂ ይወዳል መራቂ**" እንደሚባለው ሁሉ ዓይጋም ከላይ ያስቀመጠውን ዘገባ ዘባርቆ እንጀራውን ማብሰል ስለአለበት መናኛ ነገሮችን ሁሉ ጠቅጥቆ አለቃውን ማወደስ ግዴታ ተጥሎበታል - እንደ ቦንዱ ታሪክ ማለት ነው። በባዶ ሠብዕና ላይ የቆሙና የሚጥመነመኑ ሰዎች ችግር፣ ነውርን አለማወቃቸው ነው። ሥነ ምግባር፣ ሥነ ደንብ ወይም ሥነ-ሥርዓት የተባሉ አሴቶችን በሙሉ፣ ሁሌም ተፃረው ግብግብ ሲገጥሟቸው ይስተዋላሉ። ትንንሽ ጭንቅላቶች የሚያሳዝኑት ለእንደዚህ ዓይነቱ ምቾ፣ በቀላሉ የተጋለጡና የተመቹ መሆናቸው ነው።

የዜናዊ አገዛዛ ዕድፍና ጉድፍ የበዛባት አገዛዝ ነው። ይህ ብቻ አይደለም - የዚህን ጥርቅም አገዛዝ ገመና ከፍተን ብናየው በሰው ማኃል ቆሞ የሚያስኬድ አይደለም። ዕድገታቸውና ታሪካቸውም ቢጤን ደግሞ ቀና የማያስብልና የማይወላዱበት ነውና ውርደታቸውን - ጌጥ፣ ውድቀታቸውንም - አምሃ ብለው መስበክ የማንነታቸው መደበቂያ አድርገው ይጠቀሙበታል። እነኚህ ሰዎች እነዚህን ለመሠሉ ክቡር ለሆኑ እሴቶች አፅቅ ያህል ቦታ አይሰጡም። ለዚህ ነው የአገሬ ሰው **ባለጌን ካሳደገ - ያነቀው ፀደቀ** ይልና ለነውር እና ለነውረኞች ፊት የሚነሳቸው። ወጣ ወረደም፣ የአቶ ፅጌ ሃብተማርያም መፈታት በእውነቱ ከሁሉም በላይ አስደሳችና ለወዳጅ ዘመድ

ሆነ ለመላው ቤተሰብ በሙሉ፣ እንኳን ደስ አላችሁ ስል ከልብ ነው። ግን ይህ ጉዳይ በዚህ ያቆማልን.....? አሁንስ ቢሆን በእሳቸው እግር **"በሽብርተኝነት"** ስም ስንቶች ወደ ዝብጥያ አልተወረወሩም...? ወያኔስ ይሄንን መሳይ አጋጣሚ እንዴት ይጠቀምበታል...? እንዴትስ ሲጠቀምበት ቆየ... ? እኛስ ፀረ ወያኔ ነን የምንለው **"*ታጋዮች*"** እንዴት አስተናገድነው...? እንዴትስ ተጓዝንበት ...? ብለን አንድ በአንድ አካሄዳችንን ብንፍተሽና ራሳችንንም ብንገመግም ሕፀፃችንን ቅልብጭ አድርገን ማዬት ይቻለናል ነው። በሽታችንንም አውቀን ከመድኃኒቱ ጋር እናገናኘዋለን - **"በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም"** ይባላል።

የተከብራችሁ አንባቢዎች !

*ወያኔ እስካሁን ድረስ እየገዛ (ነፍሱን በቀጭን ክር አንጠልጥሎ የያዘት እንበል) እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንድ አዘናጊዎች እንደሚሉን በጥንካሬው ሳይሆን፣ ፍርኃቱ በሚወልደው ጭንቀቱ አስገዳጅነት መሆኑን ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ ወይም ከአገዛዙ ጋር መሥራትን ግድ አይለንም። ይህ አንድ ሐቅ ነው። እንደእኔ እንደእኔ ወያኔ በእውነቱ ደካማ ነው። በነገራችን ላይ ከእንስሳት ሁሉ የመጨረሻ ፈሪ ዝንጀሮ እንደሆነ ታውቃላችሁ...? የወያኔ ድፍረትም የዝንጀሮ ዓይነት መሆኑን፣ የሚያውቁት ያውቁታል - ግን አልተፈተነም።*

ይህችን ወያኔ ነፍሱን ያንጠለጠለባትን ቀጭን ክር በጥሰን እንዳንጥል ደግሞ ከፊታችን እየመጡ የሚደነቀሩ እንቅፋቶች አልታጡም። በእውነቱ ችግራችን ሁሉ ወያኔ ብቻ ነው ማለት አይቻለም፣ አይደለምም። ለእኔ ወያኔ ችግር ሳይሆን <u>**ጠላት**</u> ነው። ችግርማ የቤት ልጅ ነው። በየትኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ችግርና ሃሳብ ምንግዜም የሚኖሩ ናቸው፣ አይጠፉም። ወያኔ ግን ከችግራችንና ከችግር በላይ ነው። ይህ ሃቅ ሆኖ ሳለ ታዲያ፣ እንደ መኸገር የተጣበቀውን ጠላት ማርከሻውን እንዴት አጣንልት ብለን ከጠየቅን፣ ሁላችንም በየጓዳችን የምናገኘው መልስ፣ ማርከሻውን ደብቀን አብዛኛዎቻችን በባዶውና ለታይታ ብቻ የምንጮህ በመሆናችን ነው። እስቲ ከብዙ ችግሮቻችን ውስጥ ዋና ዋናዎችን በጥቂቱ ለማሳየትና ለመዳሠሥ ልሞክር።

*ወያኔ ኢትዮጵያን እያተራመሠ በሥልጣን ለመቆየት አገዛዙን ሲተክል፣ ከቀን አንድ ጀምሮ አገዛዙን ያደላደለው በዜጎቻችን ህይወት ላይ እየተራመመደ ለመሆኑ ለሁላችን የተሰወረ አይደለም። ማሰር ብቻ ሳይሆን የዜጎቻችንን ህይወትንም እየቀጠፈና እየሠወረ እስከአሁኗ ደቂቃ ድረስ ሊቀጥል እንደቻለ አሌ ማለት አይቻልም። እነ ተስፋዬ ታደሰን ያስታውሷል። ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ታሥረው ደብዛቸው የጠፋው የኢሕአፓ አባላት በሙሉ፣ ዛሬም ድረስ ወያኔን ተቃዋሚ ነን በሚሉት ኃይሎቻችን ሁሉ* <u>**የት ደረሱ?**</u>**፣** *ተብሎ የማይጠየቅና የማይደፈር ተራራ ሆኗል። ግን ነፃነትን ደግሞ እንፈልጋለን። በመሠረቱ የእነኝህን የት እንደደረሱ ያልታወቁ ዜጎቻችንን መዳረሻ መጠየቅ ማለት፣ አዕምሮውን ገልጦ ለሚያስብ ህሊና፣ ቢያንስ የፍትህን ሚዛን ፈልጎ ለማግኘት የመጀመሪያውን እርምጃ ተራመደ ማለት ነው። ተከታዩ ደግሞ ፍትህን በእጅ ለማስገባት ሩጫ ላይ መሆኑን ማሳያ ነው።*

በጣም የሚያሳዝነው ግን ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ እንኳን፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ነን ብለው እንድንቀበላቸው ብዙ ያስገደዱንና የተፍጨረጨሩ **"*ታጋዮቻችን*"** ሁሉ**፣** ዛሬም ድረስ የእነ ፀጋዬንና የበርካታዎችን የኢሕአፓ አባላት እስረኞች የት ደረሱ ብለው፣ ደፍረው ሊጠይቁ አልተቻላቸውም። ይሄ በጣም አሳዝኝ እና እንደዜጋም የሚያሳፍረን ሊሆን ይገባል። እንደሚመስለኝ ለእነዚህ **"*ታጋዮቻችን*"** የኢሕአፓ እስረኞች ማለት ያውም (ለእያንዳንዱ ዜጋ መብት መከበር ሲታገሉ በወያኔ እጅ የወደቁትን)ሁሉ ኢትዮጵያዊ አይደሉም፣ ዜጋም አይደሉም ማለት ነው። ይሄ ታዲያ እንዴት አያሳፍረም...? ወያኔ ስለእነ ደብተራው አስሮ አልናገር ማለቱ እየገረመን ባለበት ሁኔታ፣ በዚህ በኩል ደግሞ የእኛ የምንላቸው ሰዎች 20 ዓመት ሙሉ እነ ደብተራው የት ደረሱ ብሎ ለመጠየቅ አፋቸው ሲሸበብ ምን ሊባል ይችላል ወገኖቼ ...?

አሁን፣ አሁንማ እስርን ራሱን ልብስ እንድናደርገው ከለገሠ ዜናዊ ባልተናነስ ሁኔታ፣ ጅዋጅዌ የሚጫወቱበት ሰዎች በርካታ ናቸው። የሠብዓዊ መብት ተሟጋች ወይም (human rights activist) ነን የሚሉን፣ ነገር ግን ግብራቸው ከስሙ ጋር የማይገጥም አያሌ ግለሰቦች፣ እዚህ በምንኖርበት ባዕድ አገር ውስጥ እንዳሸን ፈልተዋል -ይህ የሚያስገረም አይደለም። የአንዱ ሞት ለሌላው ክብረት እንደሚባለው መሆኑ ነው። እነርሱም ቢሆኑ ታዲያ  የኢሕአፓ እስረኞችን ሰም ማንሳት ቀርቶ "**አሰተባበርነው**" በሚሉት ሠልፍ ሁሉ ሳይቀር፣ የእነ ደብተራውን ፎቶ መያዝ እየተቸገሩ ስናይ፣ ምንኛ የሕዝባችንና የኃገራችን እጣ ፋንታ በድቅድቅ ጨለማ ውሰጥ እየተንፏቀቀ እንደሚቆይ እናስብና ኃዘናችን ልክ ያጣል።  ሌላም አለ - እነኝሁ ሰዎች ወያኔ በዘር ከፋፈላን እያሉ  ሲያላቃቅሱ እናይና መልሠው ግን እነርሱ ደግሞ በወያኔ ሰለባ የሆኑ የጋራ እስረኞቻችንን በድርጀት አጥር ከልለው የእከሌ፣የእከሊት በማለት በየፊናችን በር ዘግተን እንድናለቅስና እንድንላቀስ ሲያደርጉን መመለከት አጀብ የሚያሰኝ ነው _በጣም አሳዛኝ!።

ኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን በዜግነታቸው እንዳይኖሩ ወያኔ የሚያደርስባቸው ጫናና እንግልት ሳያንሰን፣ እዚህ ደግሞ በሠብዓዊ መብት ወይም (human rights activist ነት)ስም ራሳቸውን የሾሙ ግለሰቦች፡ የጋራ እስረኞቻችንን በመከፋፈል ለወያኔ ሰለባ እንዲሆኑ ማድረግ ፈፅሞ ኃላፊነት የጎደለውና፣ አደገኛ አካሄድ በመሆኑ በግልፅ ሊነገራቸውና አቁሙ ሊባሉ ይገባል እላለሁ። በሰው ነፍስ መቀልድ መቆም መቻል አለበት።

80 ሚሊዮን ህዝብ ዛሬ በኢትዮጵያችን በግርግም ውስጥ እየኖረ እንዳለ ከማንም የተሠወረ አይደለም። የሆኖ ሆኖ ለዜጎቻችን መታሰር፣ በድብቅ መሠወር፣ መገደል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ወያኔን በሚጠቅም መንገድ የሚራመዱ፣ ኃይሎች አሉ። ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ዜጎች በድብቅ በወያኔ እየታደኑ ሲሰወሩ መቆየታቸው እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ደግሞ ከምርጫ 97 በኋላ እንደ አዲስ አገርሽቶ፣ በግልፅና በአደባባይ ብዙ እስረኞችን ኢትዮጵያችን አስተናግዳለች። እንደዚያም ሆኖ ግን ብዙዎች ስማቸው የማይጠራ፣ የማይነገርላቸው፣ ለሽልማት የማይታጩ ወይም ያልታጩ ይሁኑ እንጅ በወያኔ እስር ቤት ግን መራራውን ፍዳ እየተቀበሉ ናቸው። እውነታው ይሄ ሆኖ እያለ፣ ብዙ ዜጎቻችንም በኢትዮጵያ እስር ቤቶች  በር ተዘግቶባቸው የፍትህ ያለህ በሚሉበት እውነታ ፣ በጣም በሚያሳዝን መልኩ መቶ (100) እስረኞች ብቻ ነው ያሉት ተብሎ፣ ሲነገርም አዳምጠናል። በዚህም ሳቢያ ነፈሰ ገዳዩን ወያኔ ትንፋሽ እንዲያገኝ ረድተነዋል።

ጨካኙ መለስ ደግሞ ይሄንን አጋጣሚ ይወደዋልና ዜጎችን ለማሰርና፣ ለመሰወር በገፍ ይጠቀምበታል -ተጠቅሞበታልም። ይህ ብቻ አይደለም። የእነኝህን (Activist) ነን ባዮችን ልክ ያውቃልና፣ ትኩሳታቸውን ለመለካት ወይም ለማስጮህ ሲፈልግ ደግሞ በጥቃቅን ነገሮች እያስታከከ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሰኘው ጊዜ ዜጎችን ስም ለጥፎ ያስራል - ባሰኘው ጊዜ ደግሞ ፈርማችሁ ውጡ ብሎ በዜጎቻችን ሕይወት ላይ ገበጣ ይጫውታል፣ ይሳለቃል። ይህ አሳዛኙ ገፅታ ነው። ዊኪሊክስ በዚህ ጉዳይ ላይ ዝረዝር ዘገባ ይዞ ወጥቷል፤ አስገራሚ የሆነውን ግን ቀንጭቤ ለማሳየት እሞክራለሁ።እንዲህ ይላል፥

> "በአሜሪካ የሚገኙ አክራሪ የቅንጅት ደጋፊዎች ለአሜሪካ አምባሳደ ከሚያደርሱት ስደብ አዘል የስልክ ንግግሮችና የኢ-ሜይል መልዕክቶች መረዳት የሚቻለው፣ አሜሪካ የሚገኙ የቅንጅት <አክራሪዎች> የእስረኞች በእስር የመቆየት ሁኔታ ጠ/ሚንስትሩን ለማጥቃት የተሻለ መንገድ እንደሆነ የሚያስቡ ናቸው - ምክንያቱም ለእነርሱ የእስረኞቹ መፈታት የኢትዮጵያን መንግሥት የሚቃወሙበትን ሌላ መንገድ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋልና። "... ይላል የዊኪሊክስ መረጃ!።

ዊኪሊክስ ይሄን በተመለከተ ዘገባው ሰፊ ነው። እኔም የዊኪሊክስን መረጃ የሚያጠናክር አንድ ተጨባጭ ነገር ልጨምር። አንድ ሰሞን በካናድ እኖራለሁ የሚል አንድ ግለሰብ፣ ራሱን ለመደርከ ወይም ለእይታ ለመሸጥ ሲል "**ብርቱካንን አሁን ዜናዊ መፍታቱ**" የምንታገልበትን ወይም የምንጮህበት አጀንዳ ያሳጣናል እና በእኔ በኩል አሁን መፈታቷ አልተመኘም ሲል፣ አሳፋሪ ፅሁፍ በደረ-ገፆች ለቆ አስነብቦናል። ግን በዚህ አሳዛኝ ገፅታ መኃል የዜጎቻችን ህይወት ያላግባብ ሁሉ ይቀጠፋል። ደግምም ስማቸው የማይጠራ፣ የማይሰተ ጋባላቸው። ሌላም አለ። በ1997 ምርጫ ወቅት ያኔ አዲስ አበባ በፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ "**<u>ድምፃችን ይከበር፥ ሰዎቻችንን አሳልፈን አንሰጥም</u>**" ብለው እሳት ከሚተፋ ጠመንጃ ጋር ተጋፍጠው ስለተገደሉት 5 ወጣት ጀግኖች፣ እስከ ዛሬ ማንም ሰው ስማቸውን አንስቶ የሚፅፍ ወይም የፃፈ አልታዬም። 8 ዓመት ሙሉ - ከ1997-2004 ዓ.ም -ዓይገርምም!

በአንፃሩ ግን በእነርሱ ሞት ዝናን ያገኙና "**እንቱ**" የተባሉ ሰዎች በባዕድ አገር በሽ ናቸው። ለ15 ዓመት ያህል የት እንደነበሩ የማይታወቁ ግለሰቦች ሳይቀር፣ ወደ አደባባይ ብቅ፣ብቅ ብለው ከእነዚያ ጀግኖች በላይ በየድረ-ገፁ እና አዲስ አበባም ብልጭ ድርግም በሚሉ ጋዜጦች ሁሉ ሳይቀር ፎቷቸውን ያስለጥፋሉ፣ ይለጥፋሉ ጉድ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ በ"**ሽልማት**" እየታጀቡም ታሪክ የሠሩ ጀግኖች በመባል 8 ዓመት ተወድሠዋል፤ መፅሀፍ ፃፍን እያሉም ብዙ ገንዘብ ከተዋል። ይህም አሳፋሪ ታሪካችን ነው።

እነኝህ 5 ወጣቶች ሕይወታቸውን ለእኛ ቤዛ ሲያደርጉ መልዕክታቸው በጣም ግልፅ ነው። ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ደግሞ በወያኔ መቃብር ላይ ፍትኃዊ የሆነ የሕግ ተቋም ለመገንባትና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይተዳደር ዘንድ ካላቸው ምኞት እንደሆን ጀግንነታቸው ይመሠክርልናል። ይህንን ደግሞ በአፋቸው ሳይሆን በተግባር - **እደግመዋለሁ**፣ በአፋቸው ሳይሆን በተግባር - ከመረጧቸው ሰዎች በፊት ግንባር ቀደም ሆነው ውድ ሕይወት በመክፈል ጀግንነትን አሳተምረውናል። እነዚህ ወጣቶች እንደዚያኛው እንዳለፈው ትውልድ ጀግኖች፣ ጀግነው ያጀገኑን ዕንቁዎቻችን ናቸው። የኢትዮጵያ ጀግኖች ናቸውና ሁሌም በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ እንደ ወርቅ ነድ ብርሃን የሚሰጡንና የሚያላብሱን ***<u>ፀጋዎቻችን</u>*** ናቸው።

ሌላም እውነት ልጨመር። በዚሁ በ1997 ምርጫ ወቅት በዚያው ዕለት በአፍላው፣ አዲስ አበባ አሁንም **<u>የወላጆቻችን ድምጽ ይከበር</u>** ብለው በወጡ ወጣቶች ላይ የወያኔ አገዛዝ ባዘነበው ጥይት ከተገደሉት ውስጥ የመጀመሪያዋ ጀግና፣ ሽብሬ ደሳለኝ መሆኑዋ አይዘነጋም። ሽብሬ ከቤቱዋ እንደወጣች ሳትመለስ በአሰቃቂ ሁኔታ በአጋዚ ጥይት ተደብድባ ህይወቷ እንዳለፈ በማግስቱ፣ እዚሁ በምንኖርበት ባዕድ አገር ውስጥ የዚህችን ወጣት ልጅ ፎቶ ግራፍ በድረ-ገፆቻቸው ላይ ለጥፈው በስሟ ገንዘብ የሰበሰቡና ወደ ኪሳቸው የከተቱ "**የዚያን ጊዜ *ታጋዮች***" ብዙ እንደነበሩ ዛሬ እየሰማን ነው:: የገበያ ግርግር እንዲሉ አንዳንዶችም አሜሪካ ውስጥ በዚያን ወቅት ገንዘብ በመቦጨቅ የግላቸውን ራዲዮ ከፍተው ዛሬ መተዳደሪያቸው ያደረጉ፣ ግለሰቦች የሚያዙበት፣ የሚናገሩበት፣ የሚወደሱበትና "**እንቱ**" የተባሉበት ሁኔታ እንዳለ እንመልከታለን - ራዲዮ በኪስ እስኪመሰል።

እነ ሽብሬም በእውነቱ ለዚህ አልነበረም ሕይወታቸውን ቤዛ ያደረጉት። የእነ ሽብሬ ዋና ጥያቄ "**የሕዝባችን ድምፅ ይከበር**" የሚለው ሆኖ ሳለ ያን የእነርሱን ድምፅ ደፍቀንና አውርደን በ"***መሪዎቻችን ይፈቱ***" በሚል እንዲተካ የተደረገው ሆን ተብሎ በዕቅድ ለመሆኑ ዋቤ ማቅረብ አያሻም። ይህ ሲባል ግን አሁንም ቢሆን መሪም ሆነ ተራ ፣ማንም ዜጋ (አላግባብ የታሰረ ሰው)ን እንዲፈታ መጮህ የለብንም ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ይህ አቅጣጫን የማሳትና ከሃዲዱ እንዲወጣ የማድረግ ተግባር የወያኔ ብቻ ነው ለማለት ግን ያስቸግራል።

የሠብዓዊ መብት ተሟጋች (human rights activist) ስሙ ብቻ ራሱ እጅግ ያማልላል። እንደስሙ ሁሉ ተግባሩና ግዝፈቱም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው። ይህ ከሆነ ዘንዳ በባዕድ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በሙሉ ታዲያ በዚህ ተቋም ሥር ተሠልፎ ተገቢ ሚና ቢጫወት በእውነቱ ከማንም በላይ ተጠቃሚው ራሱ ሆኖ ሳለ ለምን ብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ ሊሸሸው ፈለገ…? ችግሩ ምን ይሆን.?

ነገሩ እንዲህ ነው ። የሠብዓዊ መብት ንቁ ተሳታፊ ወይም human rights activist ነን ብለው የቆሙ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን፣ ለዚህ ለሚሉት ለሠብዓዊ መብት መረገጥ እንታገላለን ሲሉ መተከላቸው/principle አድርገው የሚራመዱበት መንገድ፣ ፍፁም የተሳሳተ መሆኑ ነው። ይኸውም "**የእኛ ወይም ምርጥ ሰዎቻችን**" የሚሏቸውን ብቻ መሠረት አድርገው ለመንቀሳቀሳ መፈለጋቸውና ማቀዳቸው ነው ዋና ህፀፁ። ግን የዓለም ዓቀፍ ሠብዓዊ መብት ድንጋጌ ደግሞ ይሄንን መሠል "**ምርጥ ሰዎች**" የሚል ሐረግ በማከል ሰዎችን መለየት (ኢ-ሠብዓዊ አመለካከት)ነው ብሎ አምርሮ ያወግዛል፣

ሠብዓዊ መብት(human rights) እና የአካባቢ የአየር ብክለት (environmental polition) ማለት ድንበር የማያግዳቸው ወይም የማይከልላቸው የሰው ልጆች የአስተሳሰብ ውጤቶች ናቸው። በአንፃሩም እነኝህ ሁለት መሠረታዊና ጥልቅ የሆኑ የሰው ልጅ እሳቤዎች በማንኛውም ሰው **<u>ሆን ተብለው</u>** ከተገደፉ ማለትም ከተዳጡ፣ ማንኛውም ሰው ለሠብዓዊ መብት እታገላለሁ የሚለውን እሳቤ ወይም የሰውን ልጅ ሰብዓዊነት ተፃረር ማለት ነው። ሰዎች እነኝህን መሠረታው ጉዳዮች **<u>እያወቁ ግን አስበው</u>** ከእነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ፅንሰ -ኃሳብ ሲያፈነገጡና ሲወጡ፣ የሚሠሯቸውና የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴያቸው በሙሉ ወርቅ መሳይ አርቲፊሻል መሆናቸው ሳይውል ሳያደር የአደባባይ ምስጢር ይሆናል ማለት ነው።

አንድ ሰው ሠብዓዊ ለሆኑ መብቶች ለመታገል ሲነሳ በሕሊናው የሚጠየቀው ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ብቻ ነው - ፈቃደኝነቱና በተፈጥሮው ለሰው ልጅ ሥስ ልብ ያለው ወይም ያላት መሆኑ/መሆኗ ብቻ በቂ ነው። የእያንዳንዱ ሰው ሕሊና እነኝህን ሁለት ነገሮች ይዞ ባልተነሳበት ሁኔታ፣ ተግባሩ ሁሉ የአፍ ላይ ነፋስ ይሆንና ይህንንም ክቡር ተግባር ማለትም ለሰው ልጅ ሠብዓዊ መብት መታገልን፣ ሰው ሁሉ እንዲጠላው ያደርጋል ማለት ነው፤ ይሄ ታዲያ ወንጀል አይሆንም…? የአየር ብክለትም እንደዚያው ነው። የአንድ አካባቢ የአየር ብክለት የዓለምን የአየር ሁኔታና ደህነነት ይነካል የሚባለውም ለዚህ ነው። በዚሁ ዓይን በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ በአንድ አካባቢ የሠብዓዊ መብት መጣስ -በየትም ሌላ አካቢቢ ሠብዓዊ መብት መጣስና መረገጥ ነው የሚለውን መርህ አፅኖዖት ሰጥቶ የሚራመደው SOCEPP፣ ቀዳሚ መፈክሩ አድርጎ የያዘውና የሚያስተጋባውም ለዚህ ነው።"**<u>Injustice Anywhere is Injustice Everywhere</u>**" ሲል ክቡር ዋጋ ለመሥጠት ፈልጎ ይመስለኛል።

ይህ የ SOCEPP አቋም የአፍና የማስመሰል ቢሆን ኖሮ 16 ዓመት ሙሉ ራሱን ችሎ SOCEPP ህልውናውን ጠብቆ መቆየት ባላስቻለው ነበር። በነገራችን ላይ SOCEPP የተቋቋመው ከዛሬ 16 ዓመት በፊት ሲሆን፣ ዓላማውም ኢትዮጵያ ውስጥ የተረሱና በእሥር የሚማቅቁ ዜጋዎችን መታደግ፣ የመሠረቱ ድንጋይ አድርጎ ሲሆን፣ ቀለሙ ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሆነ ተቋም ነው። ከ1986 ዓ.ም(የኢ.አቆጣ.) ጀምሮ ከሰሜን እስከ ደብብ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ዘር፣ሃይማኖት፣ ፆታን ሳይለይ በፀረ-ኢትዮጵያው አገዛዝ (ወያኔ) ሰለባ ለሆኑ ኢትዮጵያኖች በሙሉ ለሁሉም በእኩል ሲያነባ፣ ሲጮህና ሲያስተጋባ የቆዬ ተቋም ነው። አሁንም ይሄንኑ እያደረገ ይገኛል። ለሠብዓዊ መብት እታገላለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ የSOCEPP ን ዓርአያ መከተል ይኖርበታል፤ ቢያንስ ቢያንስ ታማኝነትን ከሕዝብ ለማግኘት የSOCEPP ዓርአያነቱ አንድና ሁለት አይባልም። ጨረስኩ።

**የሕዝብ ትግል ያሸንፋል! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞ በሙሉ ይፈቱ!**
**ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኖር!**

**ቸር ይግጠመን**
October 4/2012